# የኢትዮጵያ ክልሎች አደረጃጀት እንደገና ቢከለስስ (Redraw ቢደረግስ)?

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ

08-01-15

## መግቢያ

የፌዴራል ስርአት በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ከተደገፈ አዳዲስ ለውጦችን የማስተናገድ ብቃት እንዳለው ይታመናል፣ የህዝቡን ፍላጎትና የአስተዳደር አመቺነትንም ግምት ውስጥ እንደሚያስገባም በተግባር የተረጋገጠ አውነት ነው፣ የፌዴራል ስርአትን ከሌሎች የሚለየውም በአንድ ወቅት የተሰራው አከላለልና የተደራጀው አስተዳደራዊ መዋቅር ለዘላለም ሳይነካካ እንዲኖር ሁኔታው የማይፈቅድ ይልቁንም የህዝብን ፍላጎት ታሳቢ የሚያደርግ ለውጥ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ይህን የምንልበት ዋነኛው ምክንያት ደግሞ እንደ አንዳንድ የፖለቲካ ሳይንስና የፌዴራሊዝም ምሁራን እምነት ከሆነ የፌዴራል ስርአት በባህሪው ሁል ጊዜም ቢሆን በለውጥ ሒደት ውስጥ የሚገኝና በአንድ ወቅት ተሰርቶ ሊጠናቀቅ የማይችል የፖለቲካ ስርአት ስለሆነ ነው (Federal Political System by Its Nature is Dynamic and Unfinished Project)፡፡

ስለሆነም በአለማችን የፌዴራል ስርአትን በሚከተሉ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ አደረጃጀቶች በየጊዜው የሚፈጠረውን አዳዲስ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ መለዋወጣቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርአትም የዚህ መሰረታዊ መርህ ተጋሪ በመሆኑ አዳዲስ አስተሳሰቦችንና ፖለቲካዊ ለውጦችን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል እንጂ የዚህ አይነት ጥያቄዎችን እንደ የስጋት ምንጭ አድርጎ ሊመለከት አይገባውም፣ በመሆኑም ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግን ጨምሮ አጋር ድርጅቶቹ ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ለጊዜው የተዳፈኑ የሚመስሉ ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ ተብላልተው ሳይታሰብ ሊፈነዱ የሚችሉ የብሔር-ብሔረሰብ ጥያቄዎችን አንዳንድ ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ቡኖች ያለ አግባብ ሳይጠቀሙባቸው በጥናት ላይ ተመስርተው ፍትሀዊ በሆነ መልኩ መመለስ እንዳለባቸው ይታመናል፡፡

በዚህ ረገድ ቀደም ሲል በሌላ መጣጥፌ ላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደሞከርሁት የህንድና የናይጀሪያ ፌዴራል ስርአቶች ተሞክሮን በአግባቡ መመልከቱ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ህንድ እ.አ.አ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ የፌዴራል ስርአትን ተግባራዊ ማድረግ ስትጀምር የነበረውን አስተዳደራዊ አደረጃጀት ለማስተካከልና በዚሁ ሳቢያ ተፈጥረው የነበሩትን ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሰብአዊና ሀይማኖታዊ ቀውሶችን በመፍታት ዘላቂ ሰላምንና የተሻለ መረጋጋትን ሊያስገኝ የሚያስችል አደረጃጀት ለመፍጠር በማሰብ ራሱን የቻለ የመልሶ ማደራጀት ኮሚሽን አቋቁማ ቀደም

መጀመሪያ ተዋቅሮ የነበረውን አደረጃጀትና የድንበር አከላለል እንደገና በመፈተሽ በአዲስ መልክ እንዲሰራ አድርጋለች፡፡

በዚህም መሰረት የህንድን ማህበረሰባዊ አደረጃጀትና የሀገሪቱ ህዝቦች የሚናገሯቸውን ቋንቋዎች ግምት ውስጥ ያስገቡ ሀያ ስምንት ክልሎች በአዲስ መልክ እንዲደራጁ አድርጋለች፡፡ ናይጄሪያውያን ፖለቲከኞችም ቢሆኑ በአሁኑ ወቅት ከሚገባው በላይ እንዲለጠጥ አደረጉት እንጂ የክልሎችን አደረጃጀትና ቁጥር በየጊዜው በመፈተሽ የህዝብ ቅሬታዎችን በሚመልስ አሊያም ለአስተዳደር አመቺ በሆነ መልኩ አደረጃጀታቸውን ለመከለስ ሞክረዋል፡፡ በእርግጥ የናይጀሪያው የክልሎች አደረጃጀት እንደገና የተከለሰው የወታደራዊው መንግስታት መሪዎች በወሰዱው ተከታታይ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ተመስርተው የተፈጸሙ ስለነበሩ እንደ ህንድ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን በሚያበረታታ መልኩ የተከናወነ ነበር ለማለት ያስቸግር ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያም ብትሆን ፍጹም አህዳዊና የተማከለ አስተዳደራዊ ስርአት እየተከተለች በነበረችበት ወቅት ሳይቀር በተለያየ ጊዜ የአካባቢ አስተዳደር አደረጃጀቷን እያስተካከለች እንደመጣች ይታወቃል፡፡ ራቅ ያለውን ጊዜ ትተን ከአጼ ሀ/ስላሴ አስተዳደር ወደ ስልጣን መምጣት በኋላ ያለውን ሁኔታ ብንመለከት እንኳ በንጉሱ የመጀመሪያ ስልጣን አመታት ቀደም ሲል በአውራጃ ደረጃ ተደራጅተው የነበሩትን 34 የአስተዳደር አካባቢዎች ወደ ተወሰኑ ማዕከላት በማሰባሰብ በ1942 ዓ.ም አካባቢ በ12 ጠቅላይ ግዛቶች እንዲደራጁ የተደረገ ሲሆን የ25 አመት የንግስና የብር ኢዮ በልዩ በአል አከባበራቸውን ተከትሎ ደግሞ ኤርትራን በመጨመርና የሀረርጌ ጠቅላይ ግዛትን ለሁለት በመክፈል የባሌ ጠቅላይ ግዛት ራሱን እንዲችል የሚያደርግ ውሳኔ በመወሰናቸው ምክንያት በአጠቃላይ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛቶች እንዲፈጠሩ መደረጉ ይታወቃል፡፡

በደርግ የመጨረሻ የስልጣን አመታት ማለትም በ1980 ዓ.ም የወጣውን ሶሻሊስታዊ ህገ-መንግስት መሰረት በማድረግም ቀደም ሲል የነበሩትን አስራ አራት ክፍል ሀገራት አብዛኛዎቹን በመከፋፈል የተወሰኑትን ደግሞ የራስ ገዝ (ለምሳሌ ኤርትራ፣ ትግራይ፣ አሰብ፣ ኦጋዴንና ኢሳ) እና በሀያ አምስት የአስተዳደር አካባቢዎች ተከፋፍላ የተደራጀችበት ሁኔታ የነበረ መሆኑም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በዋነኛነት በኢህአዴግ መራሹ ሰራዊት አማካኝነት የደርግ መንግስት ከስልጣን መወገዱን ተከትሎ የተቋቋመው የሽግግር መንግስት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 7/1992 ዓ.ም አማካኝነት አዲስ አበባን ጨምሮ አስራ አራት ክልሎችን በማዋቀር ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ለእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ሆኖ የነበረውን የብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደርና የእኩልነት ጥያቄን በመሰረቱ ለመመለስ ሞከረ፡፡

ሆኖም ብዙም ሳይቆይ አስተዳደራዊ ወጭን ለመቀነስ በሚል ሽፋን የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ክልል የፈጠሩት አምስቱ ክልሎች ፖለቲከኞች ህዝቦቻቸውን በአግባቡ

ሳያማክሩና በንቃትም ሳያሳትፉ እንዲሁም በወደፊት ሁለንተናዊ ህይወታቸው ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ፖለቲካዊ ችግር ሳያገናዝቡ በወቅቱ የነበረውን የኢህአዴግ አመራር ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ ብቻ ተስማምተው ወደ አንድ በመምጣታቸው የክልሎች ቁጥር ወደ አስር ዝቅ ያለበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በመጨረሻም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በተለየ መልኩ የፌደራል መንግስት ከተማ ሆኖ እንዲደራጅ ከማድረጉ ውጭ በሽግግር መንግስት የተደራጁት ክልሎች በህገ መንግስቱ ባሉበት ሁኔታ እውቅና እንዲያገኙ ተደርጎ ዘጠኝ ክልሎች ሆነው እንዲቀጥሉ ተወሰነ፡፡

ስለሆነም ከላይ በምሳሌ አስደግፌ በአጭሩም ቢሆን ለማሳየት እንደሞከርሁት በፌዴራል ስርአት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተለምዶ አሀዳዊ እየተባለ በሚጠራው መንግስታዊ ስርአት እንኳ የአካባቢ አስተዳደራዊ አደረጃጀቶች ሁኔታ በአንድ ወቅት በተወሰኑ ፖለቲከኞች ፍላጎትና ስምምነት ተሰርቶ የሚያልቅና በዚያውም የሚያቆም ሳይሆን በየጊዜው እየተፈተሸ ጥቅሙና ጉዳቱ የሚለይበትና በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊስተካከል የሚገባው ጉዳይ ካለ በጊዜው እየተስተካከለ የሚሄድ መሆኑ ላይ አሁን በስልጣን ላይ የሚገኙት ፖለቲከኞችም ቢሆኑ በጽናት ሊያምኑበት የሚገባው እውነት ይመስለኛል፡፡

ለዚህም እኮ ነው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት ይህንን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በክልሎች ውስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች በማንኛውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል ሊያቋቁሙ ይችላሉ በማለት ፈቃጅ የሆነ ድንጋጌ ያሰፈረው፡፡ በሌላ አገላለጽ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት በአንቀጽ 47 (2) ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱት ክልሎች ውስጥ የተካተቱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በማንኛውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው ሲል በማያሻማ አኳኋን የደነገገው፡፡ በፖለቲከኞቻችን አካባቢ ያን ያህል አድማጭ ማግኘት አለመቻላቸው ነው እንጂ ኢትዮጵያዊያን ምሁራንም ከላይ የተቀመጠውን ትክክለኛ አመለካከት በሚያጠናክር መልኩ ሀሳባቸውን በግልጽ ሲያራምዱ እንደነበረም ይታወቃል፡፡

በዚህ ረገድ በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱት ምሁራን አንዱ ዶ/ር አሰፋ ፍስሀ ሲሆኑ Federalism and the Accommodation of Diversity in Ethiopia በሚለው መጽሀፋቸው ገጽ 265-266 ላይ *"አንዳንዶች የአማራና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች እንደገና ቢደራጁ መልካም እንደሆነ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ክልሎች በተለያዩ አዳዲስ ክልሎች እንደገና እንዲደራጁ ማድረጉ አሁን ላይ በግልጽ እየተስተዋለ ያለውን የፖለቲካ ስልጣን ልዩነት እንዲጠብ ከማድረጉም በላይ የአስተዳደር አመቺነትንም ሊያመጣ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡"* በማለት ሀሳባቸውን ከመሰንዘራቸውም በላይ በዚሁ መጽሀፋቸው ገጽ 267 ላይ የስዊትዘርላንድን ተሞክሮ ለሀገራችን በሚጠቅም መልኩ በማንሳት የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረው እናገኛለን፡፡

*የስዊዝ ፌዴራል ስርአት አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ባስገባ አኳኋን የተደራጀ ቢሆንም እነዚህ ህዝቦች የግድ በአንድ እናት ክልል እንዲጠቃለሉ ሳያደርግ በያሉበት በአግባቡ እንዲስተናገዱ ያደረገበትን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ በመሆኑም ስዊዝ ውስጥ ከሚገኙት ሀያ ስድስት ክልሎች (ካንቶኖች) ውስጥ ሰባቱ ጀርመንኛ፣ አራቱ ፈረንሳይኛና አንድ ጣሊያንኛ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከአንድ በላይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ህዝቦች የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ ልምድ በመነሳትም በኢትዮጵያ የሚገኙ ትላልቅ ክልሎችን ከፋፍሎ እንደገና ማደራጀት ይቻላል፣ በዚህም መሰረት ሶስት ወይም ከዛ በላይ የአማራ ክልሎችን፣ አራት ወይም ከዛ በላይ የኦሮሚያ ክልሎችን እንዲሁም ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ሶማሊ ክልሎችን ማሰብ ተገቢ ነው፡፡*

ሲሉ ሀሳባቸውን አጠናክረው ይገልጻሉ፣ ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳትም ዶ/ር አሰፋ ከላይ በተጠቀሰው መጽሀፋቸው ገጽ 10 ላይ ደግሞ ህንድ በ1950ዎቹና 60ዎቹ ገጥሟት የነበረው የአደረጃጀት ችግር በጥናት ላይ ተመስርታ ክልሎችን እንደገና በማደራጀቷ ፌዴሬሽኑን ከውድቀት ማዳን መቻሏን በመልካም ተሞክሮነት ጠቅሰው ኢትዮጵያም ይህን ፈለግ ተከትላ የክልሎችን አደረጃጀት እንደገና በመፈተሸ ብትከልስ የተሻለ እንደሚሆን ነው የመከሩት፡፡ በእርግጥ የህንድ የህገ-መንግስት ጉባኤ የክልሎችን እንደገና መዋቀር አስፈላጊነት የተገነዘበው ከነጻነት በኋላ ብዙም ሳይቆይ የተፈጠረውን ቀውስ በመመልከቱ እንደነበር ሮናልድ ዋትስን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ሳይንስና የፌደራሊዝም ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

በዚህም ምክንያት የህንድ መንግስት መከፈል ያለባቸውን በመክፈልና መዋኸድ የሚገባቸውን በማዋኸድ ክልሎችን እንደገና ለማደራጀት ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ በነበሩት አመታት በፌዴራል ፓርላማ አማካኝነት መለስተኛ የህገ-መንግስት ማሻሻል ለማድረግ ሁሉ መገደዱን በማስረጃነት ያቀርባሉ፡፡ በአጠቃላይ በመርህ ደረጃ ሲታይ በአብዛኛዎቹ የፌዴራል ስርአት ተከታይ አገሮች ዘንድ ክልሎችን እንደገና ለማዋቀር የሚወስደው ጊዜና ለጊዜውም ቢሆን የሚፈጥረው አሉታዊ ስሜት ሒደቱን አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ቢታመንም ክልሎችን እንደገና የማደራጀቱና ድንበራቸውንም በህዝቦች ፍላጎት ላይ ተመስርተው የማስተካከሉ ሁኔታ የግድ መፈጸም ካለበት ግን ዴሞክራሲያዊ፣ አሳታፊ እና በጥናት ላይ በተመሰረተ ውሳኔ አማካኝነት ተግባራዊ ማድረጉ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ እንደሚያመዝን አያጠራጥርም፡፡

## አሁን ላይ በኢትዮጵያ የሚገኙ ክልሎች አደረጃጀት በሚከተለው አኳኋን እንደገና ቢስተካከልስ?

አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የክልሎች አደረጃጀት በሽግግር ወቅት የተሰራ፣ በሚመለከታቸው የመስኩ ምሁራን ጥልቀት ያለው ጥናት ያልተደረገበትና የሁሉንም ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦችና ፖለቲከኞች ፍላጎት በአግባቡ ያላስተናገደ ይልቁንም አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በወቅቱ ተደራጅተው ይንቀሳቀሱ የነበሩት የተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የኢህአዴግ አባልና አጋር

ድርጅቶች አመራሮችና አባላት ጭምር በንቃት እና በብስለት እንዲሁም የእኩልነት ስሜትን በሚያስተናግድ መልኩ ተሳትፌው ሀሳባቸውን በነጻነት ያራመዱበትና ድምጻቸውንም የሰጡበት እንዳልነበር የተለያዩ ወገኖች በአንክሮ ሀሳባቸውን ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡ በወቅቱ የገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የበላይነቱን በያዘበትና የዴሞክራሲያዊ ስርአትም ቢሆን ገና በቅጡ ስራ ላይ ባልዋለበት ሁኔታ የገዥው ፓርቲ ፖለቲከኞች በተለይም የህወሀት መሪዎች ፍላጎትና ውሳኔ ይበልጥ ተቀባይነት የሚያገኝበትና ተግባራዊም እየሆነ የነበረበት አጋጣሚ ስለነበረ የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልልን የፈጠሩት አምስቱ ክልሎች ሳይቀሩ ወደ አንድነት የመጡት በወቅቱ የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩት አቶ ቢተው በላይ ከድርጅታቸው የበላይ አመራር የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል ባቀረቡላቸው የማግባቢያ ሀሳብ መሰረት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መሪዎች በሰጡት ውሳኔ አማካኝነት የተደራጀ ክልል ነው፡፡

በሌላ አነጋገር በአሁኑ ወቅት በአንድ ላይ ተካተው የሚገኙት 56ቱም የደቡብ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ መሪዎቹም ጭምር በአግባቡ መክረውና ዘክረው በአስፈላጊነቱም ላይ በሚገባ አምነውበትና ፍላጎታቸውንም በስርአቱ ገልጸው የተፈጸመ ውህደት እንዳልነበር የተቃውሞ ሀሳባቸውን በግልጽ የሚያቀርቡ አንዳንድ የክልሉ ምሁራንን ጨምሮ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይታመናል፡፡ ለዚህም ነው ከአመታት በፊት ብዙም የመልካም አስተዳደር ችግር ያልገጠማቸውና የክልሉን የፖለቲካ መዘውር እያሽከረከሩ ባሉበት ሁኔታ ጭምር የርዕሰ መስተዳድርነቱን ቦታ የወላይታው ተወላጅና የአሁኑ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማሪያ ደሳለኝ በመያዛቸው ብቻ የሲዳማ ምሁራንና ፖለቲከኞች ሲዳማ ራሱን የቻለ ክልል መሆን አለበት ብለው በብሔረሰቡ ምክር ቤት ሳይቀር ወስነውና አስወስነው አቋማቸውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጽሁፍ ለማሳወቅ ረዥም ጊዜ ያልወሰደባቸው፡፡

በምዕራብ የክልሉ አካባቢ የሚገኙ የብሔረሰብ አስተዳደሮችም ቢሆኑ የፖለቲካ ጫናው በርትቶባቸውና በድርጅታዊ ዲስፕሊን ማለትም በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አስተሳሰብ ተጠፍረው እውነተኛ እምነታቸውን እንደ ሲዳማ ፖለቲከኞች በድፍረት ተነሳስተው በግልጽ ወደ መድረክ የመወያያ አጀንዳ እንዲሆን አያድርጉት እንጂ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀምና ውስጥ ለውስጥ ሳይቀር የክልሉ ማዕከል ወደ ሆነው ሐዋሳ ከተማ ለመድረስ ሽህ ኪሎ ሜትሮችን ለምን እንድንጓዝና የምዕራብ ኢትዮጵያን ሰበርባራ ቦታዎችና በረሀዎች እንድናቋርጥ ተፈረደብን የሚል ቅሬታ በመያዝ ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም፡፡

በመሆኑም ያለፈውን ስህተት ከመሰረቱ ለማረምና የክልሎች አደረጃጀትም የብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦችን ጥያቄ በትክክል የሚመልሰ፣ የህዝቦችን ቅሬታ በተሟላ መልኩ ሊያስወግድ የሚችል

እንዲሁም የፍትህና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችልና ብሔራዊ መግባባትን ያለብዙ ውጣ ውረድና ከፍተኛ መስዋዕትነት ማምጣት የሚችል እንዲሆን ከተፈለገ ክልሎች በሚከተለው መልኩ እንደ አዲስ ቢደራጁ ጠቃሚ ይሆናል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ ይንጸባረቃል፡፡ ይህም ሆኖ ቀጥሎ የቀረበው የአደረጃጀት አማራጭ በመነሻ ሀሳብነት የሚታይ ስለሆነ በቀጣይ እየዳበረ የሚሄድ መሆኑና የገዥውን ፓርቲ ፖለቲከኞች ጨምሮ የሌሎችንም አመለካከት ለማግኘት በተወሰነም ቢሆን አከራካሪ መሆኑ አይቀርም፡፡

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ስር የሚገኙት በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ቢያንስ በአራት ክልሎች ተደራጅተው በአዲስ መልክ እንዲዋቀሩ ቢደረግ፣ በዚህም መሰረት የሲዳማና የጌዴኦ ብሔረሰብ አስተዳደሮች በአንድ ላይ ሆነው ራሱን የቻለ ብሔራዊ ክልል ቢፈጥሩና ማዕከላቸውንም ራሳቸው ተስማምተው እንዲመርጡ ዕድል ቢሰጣቸው አሊያም ሐዋሳን ማዕከላቸው አድርገው ቢቀጥሉ፣ የከምባታ፣ ሀዲያ፣ ወላይታ፣ ጋሞጎፋ፣ ዳውሮና በአካባቢው የሚገኙ ሌሎች የብሔረሰብ አስተዳደሮች በአንድ ላይ ተደራጅተው አንድ ክልል ቢፈጥሩና በራሳቸው ምርጫ ወላይታ ሶዶን ወይም አርባ ምንጭን ማዕከላቸው ቢያደርጉ፣ በምዕራብ የክልሉ አካባቢ የሚገኙት ከፋ ሸካና ቤንቺ ማጂ አስተዳደር ዞኖች ደግሞ በአንድ ላይ ተደራጅተው አንድ ክልል ቢፈጥሩና ማዕከላቸውንም ራሳቸው በነጻነት መርጠው እንዲንቀሳቀሱ ቢደረግ፣ እንዲሁም ጉራጌና ስልጤ ቀደም ሲል ከማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን አለመግባባት ከልብ አስወግደው የሚስማሙበትን ሁኔታ አመቻችቶ በአንድ ላይ ሆነው ራሱን የቻለ ክልል ቢመሰርቱ ለመልካም አስተዳደር መስፈንም ሆነ ለፈጣን ልማት መመዝገብ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲሁም በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የልዩ ወረዳዎች ወደሚቀርባቸው ክልል በራሳቸው ፈቃድ እንዲካተቱ ቢደረግ ሒደቱን ይበልጥ አሳታፊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሀዊ ያደርገዋል የሚል ጠንካራ እምነት አለ፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል በቆዳ ስፋቱም ሆነ በህዝብ ብዛቱ አሁን ካሉት ክልሎች እጅግ ትልቁ በመሆኑ ምክንያት ከ30 ሚሊዮን የማያንስ ህዝብ የሚኖርበት ከመሆኑም በላይ የቆዳ ስፋቱም በተለይም ከምዕራብ ወደ ምስራቅ እጅግ የተለጠጠና ከ350 በላይ ወረዳዎችን ያቀፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ይህን ትልቅ ክልልና ህዝብ በአንድ የአስተዳደር አካባቢ አጭቆ ማቆየቱ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ማመዘኑ አይቀርም፣ በእርግጥ የኦሮሚያ ክልል በዋነኛነት የአንድ ብሔር ህዝብ የሚገኝበት በመሆኑ አንድ ቋንቋና በአብዛኛው ተቀራራቢ የሆነ ባህል ይዞ የሚገኝ ሆኖ ሳለ ለምን ተከፋፍሎ በተለያዩ ክልሎች እንዲደራጅ ይደረጋል የሚል ምክንያታዊ ጥያቄና ለጊዜውም ቢሆን አሳማኝ ሊመስል የሚችል የተቃውሞ ሀሳብ ሊያስነሳ እንደሚችል ይገመታል፡ ፡ ሆኖም የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋውን እየተጠቀመና ባህልና ወጉን እያሳደገ በሶስት ክልሎች ማለትም ምስራቅ ኦሮሚያ፣ ማዕከላዊ ኦሮሚያና ምዕራብ ኦሮሚያ በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ

ተደራጅቶ ማዕከሉን በየክልሉ አማካይ ቦታ ላይ ወስኖ እንዲተዳደር ቢያደርግ የኦሮሞን ህዝብ በቀላሉ አንቀሳቅሶ ልማትን ለማፋጠንም ሆነ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በቅርብ እየመለሱ ማህበራዊ ችግሮችንም ጭምር በዘላቂነት እየፈቱ መሄድ ስለሚችሉ ዘላቂ ጥቅም ያስገኝ እንደሆነ እንጂ አንዳንድ የዋህና አላዋቂ ፖለቲከኞች አሊያም መሰሪ አስተሳሰብ ያላቸው ወግ አጥባቂ የኦሮሞ ምሁራን እንደሚያስቡት የኦሮሞን ህዝብ ከፋፍሎ ለማዳከም ታስቦ የሚፈጸም እንደማይሆን ታሳቢ ከተደረገ ጥቅም እንጂ ጉዳት ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም፡፡

3. የአማራ ብሔራዊ ክልልም ቢሆን ከኦሮሚያ ክልል ቀጥሎ በህዝብ ብዛቱም ሆነ በቆዳ ስፋቱ በትልቅነቱ የሚታወቅ በመሆኑ ቢያንስ በሁለት ተከፍሎ ማለትም ምስራቅ አማራና ምዕራብ አማራ ተብሎ እንደ አዲስ ቢደራጅ የክልሉ ነዋሪ ህዝብ የተሻለ ተጠቃሚ ይሆን ካልሆነ በስተቀር በዚህ ምክንያት አንዳችም ጉዳት እንደማይደርስበት አስቀድሞ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡ ፡ አሁንም ቢሆን እኮ የክልሉን ስፋትና የህዝቡን ብዛት ታሳቢ በማድረግ ለስራ እንዲያመችና የምስራቅ አማራን ነዋሪ ህዝብ በቅርብ ለማገልገል ሲባል ደሴና ደብረብርሀን ላይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እየተከፈቱ መሆናቸው ይታወቃል፣ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡
4. የኢትዮጵያ ሶማሊ ብሔራዊ ክልል በህዝብ ብዛቱ ከሌሎቹ ክልሎች ያን ያህል የተጋነነ ልዩነት የሚያመጣ ባይሆንም በቆዳ ስፋቱ ግን ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ቀጥሎና ከአማራ ክልልም ጭምር ልቆ የሚታይ ስለሆነ በአንድ ክልል ብቻ አጨናንቆ ማቆየቱ የአስተዳደር አመቺነትን የማይፈጥር በመሆኑ ቢያንስ የኦጋዴን አካባቢ ራሱን የቻለ ክልል እንዲሆን በማድረግ ለሁለት ተከፍሎ ቢደራጅ የክልሉ ነዋሪ ህዝብ የተሻለ ተጠቃሚ ይሆን ካልሆነ በስተቀር አንዳችም ጉዳት እንደማይደርስበት እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል፡፡
5. በመጨረሻም አሁን ያሉት ክልሎችም ሆኑ በአዲስ መልኩ የሚደራጁት የክልል መስተዳድሮች ቀደም ሲል በተወሰኑ ቡድኖች የተሳሳተ ስሌት ላይ ተመስርተው የተፈጠሩት የድንበር ችግሮችና በዚህም ሳቢያ የተከሰቱትን የህዝብ ቅሬታዎች በጥናት ላይ ተመስርቶ በዘላቂነት የሚፈታ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ለነገ የሚባል ጉዳይ እንዳልሆነ ከወዲሁ መገንዘቡ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ረገድ በትግራይና በአማራ፣ በአፋርና በአማራ፣ በአፋርና በትግራይ፣ በደቡብና በኦረሚያ፣ በኢትዮጵያ ሶማሊና በኦረሚያ እንዲሁም በኦረሚያና በቤንሻንጉል ጉሙዝ መካከል የሚስተዋሉት በድንበር ይገባኛል ላይ ተመስርተው የተከሰቱት ግጭቶችና በየጊዜው እየቀረቡ ያሉት እውነተኛ የህዝብ የማንነት ጥያቄዎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ እነዚህም ሁኔታዎች ከአድሎ በጸዳ አኳኋን በሰለጠነና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ በዘላቂነት ሊፈቱ ይገባቸዋል፡፡

ተጠቃሎ ሲታይ የዚህ አይነት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በመደረጉም የሀገሪቱን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ዕድል የሚፈጥርና የኢትዮጵያን ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊያበረታታ የሚያስችል አደረጃጀት ስለሚሆን እንደተሻለ አማራጭ መታየት ይኖርበታል እንጂ እንደተለመደው የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦችን ለመከፋፈል ከመፈለግ የሚመጣ የጠባቦች ወይም የትምክተኞች ሴራ ነው የሚለውንና ጉንጭ አልፋ የሆነውን የተለመደ ክርክር ወደ ጎን ትተው ሁኔታውን እንደገና ቢያጤኑት እጅግ ጠቃሚ መሆኑ የሚቀር አይመስለኝም፡፡

በመሆኑም ቀደም ሲል ከነበሩት ዘጠኝ ክልሎች ላይ አምስት ወይም ስድስት አዳዲስ ክልሎችን በመጨመር ሀገሪቱ ከአስራ አምስት በማይበልጡ ክልሎች እንደገና እንድትደራጅ ቢደረግ ቀደም ሲል በሀገሪቱ ከነበሩት አደረጃጀቶች አንጻር ሲታይ ያን ያህል የተጋነነ ለውጥ የሚያመጣ ካለመሆኑም በላይ አስተዳደራዊ ወጭውም ቢሆን ከሚያስገኘው ማህበራዊ ፍትህና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ሲታይ ያን ያህል የሚከብድ ሊሆን ስለማይችል እጅግ ተመራጭ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ከዛም አልፎ የዚህ አይነቱ አደረጃጀት የብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦችን የቆየ የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በተሟላ መልኩ ምላሽ የሚሰጥ ከመሆኑ አንጻርም ሲታይ የሚያስከትለው ተጨማሪ አስተዳደራዊ ወጭ ከዚህ ግባ የማይባል ነው የሚሆነው፡፡

በሌላ አነጋገር የዚህ አይነቱ አደረጃጀት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት የሚቀርፍና ለህዝቦቹም ማህበራዊ ፍትህን የሚያስገኝ መሆኑ ሲታይ በእርግጥም የገዥው ፓርቲ መሪዎች ትልቅ ቦታ ሰጥተው እንደገና ቢያጤኑትና ለተግባራዊነቱም አበክረው ቢንቀሳቀሱ ለራሳቸው ህልውናም ሆነ ለኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች ዘላቂ ጥቅም ፋይዳው እጅግ የጎላ መሆኑንን በቅጡ በመገንዘብ ጭምር አንዳንድ አድርባይና አስመሳይ የብሔር ፖለቲከኞችና በኢህአዴግ አባባል ትምክህተኞች ወይም ጠባቦች እንደሚሉት የሀገሪቱ አንድነትም ሆነ የህዝቦች ህልውና ይበልጥ አደጋ ላይ የሚወድቅበትም ሆነ ከአሁኑ የባሰና አላስፈላጊ የሚባል አስተዳደራዊ ወጭ የሚያስከትልበት ሁኔታ አይፈጠርም፡፡

ይልቁንም አሁን ላይ ይበልጥ እየተስፋፋ የመጣውን ሙስና በጽናት ታግሎ በማስቆምና የህዝብን መሰረታዊ ጥያቄ ፍትሀዊ በሆነ መልኩ መልሶ በሁሉም መስኩ የህዝብን ተሳትፎ በአግባቡ ማሳደግ የሚቻልበትን አሰራር ቀይሶ መንቀሳቀስ ከተቻለ በአንድ በኩል የተወሰኑ ክልሎች በመጨመራቸው ምክንያት በተወሰነም ቢሆን የሚያድገውን አስተዳደራዊ ወጭ ማካካስ የሚቻልበትን ሁኔታ በመፍጠር፣ በሌላ በኩል ደግሞ መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ማህበራዊ ፍትህን በማንገስ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የያገባኛል ስሜትን እንዲፈጥር በማድረግ አላስፈላጊ ወጭዎችንና አሁን ላይ በግልጽ እየታየ ያለውን የቅንጦት መኪኖችንና የቢሮ ዕቃዎችን በየአመቱ የመቀያየሩን ሒደት በማስቆም እንዲሁም እንደ ወረርሽኝ ሀገሪቱን እያጥለቀለቀና እንደ ሰደድ እሳት ሀብቷን እየለበለበ የሚገኘውን ልቅ የሙስና ድርጊት ጠንክሮ በመዋጋት የበጀት ጫናውን በዘላቂነት እያቃለሉ መሄድ እንደሚቻል የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በጽናት ያምናል፡፡